## <u>የክርስቲያኖች መከራ፡</u> <u>አለም ያልተገባት የእግዚአብሄር ስጦታ</u>

" በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፣ ተፈተኑ ፣ በመጋዝ ተሰነጠቁ ፣ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፣ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፤ አለም አልተገባቸውምና በምድረበዳና በተራራ፣ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ። እነዚህም ሁሉ በእምነታቸው ተመስክሮላቸው ሳሉ..." ዕብ11፡37-39

መስቀሉን ተሸክመው እንዲከተሉት ኢየሱስ ለተከታዮቹ በሙሉ ግልጽ አድርጎላቸው ነበር። (ማር 8፡34) ኢየሱስን "ብዔልዜቡል ካሉት ቤተሰዎቹንማ እንዴት አብልጠው አይሏቸውም " (ማቴ10፡25) "እኔን አሳደውኝ ከሆነ እናንተንም ያሳድዷችል" (ዮሐ15፡20) በማለት አስታውቋቸዋል።
ህይወታቸውን ይበልጡን ለወንጌል ስርጭት አሳልፈው ለሰጡ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ታላቅ መከራ እንደሚጠብቃቸው ይናገራል።ለምሳሌ ኢየሱስ ለአናኒያ ስለ ጳውሎስ እጣፈንታ ሲነግረው"እኔም ስለ ስሜ ምን ያህል መከራ መቀበል እንዳለበት አሳየዋለሁ" ሲል ይነግረዋል ። ይህ መከራ ስልት ነው። ልዩ የሆነም አላማም አለው። ይሄውም ለአለም የክርስቶስን ፍቅር መግለጥ ማለት ነው።
ጳውሎስ ይህንን ሁኔታ እንዲህ ይገልፀዋል "ስለ እናንተ በተቀበልኩት መከራ ደስ ይለኛል፤ ክርስቶስ ስለ አካሉ ስለ ቤተ-ክርስቲያን ከተቀበለው መከራ የጎደለውን በስጋዬ አሟላለው"። (ቆላ 1፡24) እንደ ፊሊጲስዩስ 2፡30 አባባል "የጎደለውን..... አሟላለው" ሲል የነበረውን መጨመር ማለቱ ሳይሆን ያለውን ስለሌሎች መሸከም ማለቱ ነው። ስለዚህ ለፊሊጲስዩስ ሰዎች አፍሮዲጡ ፍቅራቸውን በስጦታ መልክ ለጳውሎስ ይሸከማል ማለት ነው።በቆላስየስ 1፡24 ላይ ጳውሎስ የክርስቶስን መከራ ለአለም በስጋው መከራ ይሸከማ ማለት ነው። የጳውሎስ የመከራ ስልት የክርስቶስን መከራ በመሸከም ማሳየት ነው።
አንድ ሚሲዮናዊ የክርስቶስን ወንጌል በማምጣቱ መከራ ሲቀበል አለም ስታይ፣ ክርስቶስ ለእነሱ ያለውን ፍቅር ያያሉ።
አለም  የክርስቲያኖች መከራ የሚገባት ስጦታ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሄር አንዴ ሰጥቷታል። ዕብራዊያን 11፡27-38 ስለ ጥቂት ክርስቲያኖች መከራ እና አለም እንደማይገባት ያወሳል። "በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፣ ተፈተኑ ፣በመጋዝ ተሰነጠቁ፣ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፣ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ <u>*አለም አልተገባቸውምና...*</u>" እነዚህ የመጨረሻ ቃላት የሚያመለክቱት አለም የክርስቲያኖች መከራ የማይገባት ስጦታ መሆኑን ነው።ይሁንና እግዚአብሄር መስጠቱን ቀጥሏል። ለመሆኑ እነዚህ የሚሰቃዩ ቅዱሳን እንዴት ለአለም ስጦታ ሆኑ? መልሱ የሚገኘው በእምነታቸው ውስጥ ነው።እነዚህ ሁሉ በእምነታቸው ተመስክሮላቸዋል (ዕብ 11፡39)ይህም ማለት በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት ነበራቸው።መከራቸው እምነት ከማጣት የተነሳ አልነበረም። ነገር ግን የመከራቸው ዋጋ በአጭሩ በእምነታቸው ውስጥ ይገኛል ።
እንዴት?

በዕብራውያን 11 ውስጥ ተመልከቱ እግዚአብሄር አንዳንዴ በተአምራት የሚያስመልጠው በመከራ ውስጥ ነው። (ዕብ11፡27-35) ።አንዳንዴ ደግሞ በመከራ እና በሞት ይፀኑ ዘንድ እምነትን ይሰጣል ። (ዕብ11፡35-39) ። በሁለቱም እምነቶች ማለትም በሚያመልጠው እና በሚፀናው እግዚአብሄር ከነፃነትና ከህይወት በላይ የከበረ ይሆናል።

ያመለጠው "ኢየሱስ ከአገኘሁት ይበልጣል" ሲል የሞተው ደግሞ "ኢየሱስ ከአጣሁት ይበልጣል"ይላል፡፡ ይህ የእምነት ምንነት ነው፤ ኢየሱስ ከሁሉም በላይ ይታመናል ይከበራልም ፡፡ለዚህ ነው እነዚህ መከራን የሚቀበሉ ክርስቲያኖች በተለይም ሚስዮናውያን ለአለም ስጦታ የሆኑት፡፡የእነርሱ ኢየሱስ ተኮር መከራ የወንጌልን እውነት ያቅፋል፤ እርሱም ኢየሱስ ህይወት ከምትሰጠው ነገር ሁሉና ሞት ሊወስደው ከሚችለው በላይ እጅጉን የከበረ እንደሆነ ነው፡፡ምን አይነት ግልፅ ያለ የመስቀሉ እወጃ ነው? ይህ እውነት አንድ ክርስቲያን  ለአለም የሚሠጠው የላቀ ሥጦታ ነው፡፡አለም አልተገባትም፡፡ "አለም አልተገባቸውም"፡፡ይሁንና እንሰጣታለን፡፡

ኢየሱስን በጥልቀት በማወቅ መከራን በመቀበል ለአለም ሥጦታን ለማበርከት ተዘጋጅ፡፡

ፓስተር  ጆን  ፓይፐር